# ተመን



በደሳለኝ ቢራራ

# ተመን

እና ሌሎችም ግጥሞች

ደሳለኝ ቢራራ

ጥቅምት፡ 2007 ዓ.ም.

© መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።።
All Rights Reserved.

የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አስተያየት ለመስጠት:

abalomender@gmail.com

**የደን እናቱ ፀሐይነሽ አለባቸው**

**መታሰቢያ ትሁንልኝ!**

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


መልዕክተ ፍቅር .....1

መ·ሰኛ ሸ·መኛ.....3

‹ነቅሎ ’ሚጥል› .....4

አባይ እወቅልኝ.....5

ገሀነብ.....7

ፅናት .....8

ጨቀየ .....9

መከለያ.....11

የሆዳም ይት·ብሀል.....13

ቃጠሎ.....14

ድሀ ተጋባኘ .....16

ንፅፅር.....17

ክቡር ዳኛ!.....18
የቶሩ ሴራ.....19
ምሳሌ.....21
ቅናት.....24
እሸጌ መሸታ¡.....26
ተመን.....29
ማዶና ማዶ ነን.....31
እንዳያስቸግረኝ¡.....32
ገድማ.....33
ቆጨሽ እንዴ.....34
አንሸና ተነሺ!.....35
እሳቸው.....36
ራስ.....37
ዝም በል!.....39
የምርጫ ሰሞን ክስተቶች.....41

**ክንድ ርቀት የለም!**.....43
የዘንድሮ ሌባ .....44
**የወል ሚስት**.....45
**ኢትዮጵያ** .....46
**የስራሺን ይስጥሽ**.....49
**ሰገጤ** .....53
**አሳድጎ ለሰው**.....55
**አማላይ** .....58
**ደባል** .....61
**የኔ ምቹ**.....66
**እግረ - ተከሉ እረኛ**.....68
**ባገሩ መቀበር** .....71
**ፈተና በላስቬጋስ**.....72

# መልዕክተ ፍቅር

መሆንሽን አውቃለሁ
እዛ ከሊቅ ሀገር
ከቁስ ከደብተራ፣
መልዕክተ ዮሐንስ
መልዕክተ ጳውሎስ
ሌሎችም መልዕክታት
ደርሰሺ በየተራ፣
ምን ያደርጋል ታዲያ
ይህን ሁሉ ትምህርት
መፃፍ መጨረስሽ፣

እንደ ሊቃውንቱ

ቀዳሽ መርጌታዎች

ላትደቁኝ ላትቀስሽ፣

ጳጳስ መሆን ስትችይ

በልቤ ከተማ

አንድ መልዕክት አውቀሽ፡፡

# ሙሰኛ ሹመኛ

ቢወጠርም ሆዱ

ቢታሸም በሞራ

አቅማዳን ሲያለፉ፣

እንዳይንቀሳቀስ

እግሩን ተቸንክሮ

እንዳይተነፍስም

ይለጎማል አፉ።።

# ‹ነቅሎ ’ሚጥል›

ጫላን ቁንጣን ያዘው ሐጎስ እየበላ

ባረረ አንጀቱ ላይ ብርንዶ ሺንገላ

ለታመመው ሆዱ ለጎስቋላው ገላ

መዳኒት ነው ብለው

‹ነቅሎ ’ሚጥል› መላ

ቤት ማፍረሻ ላኩ ደብዳቤ ለቶላ፡፡

መንበር መረን ለቆ ብያኔ ቅጥ ሲያጣ

ህሊና ሲደፈር ሞራልም ሲቀጣ

አበበም ሰከረ ጎይቶም እየጠጣ፡፡

# አባይ እወቅልኝ

እወቅልኝ አለኝ ‹አዞ ተጠማዞ›
እሱሚያውቅ መስሎ፣

ያላወቅሁት እንደሁ
ሀገር ሊቀበለኝ እንቆቅልህ
ብሎ፣

ምን አውቅልህ ብየ
ሀገር ሳላመጣ፣
አስፋልት ነው ብለው
የጠየቀኝ ጣጣ፣
ወንዝ አረገው መልሱን

ንዶቱን ሊወጣ፡፡

አንድ አገር ልሰጠው

ድጋሜ ጠይቆ፣

‹አታላይ›ን ፈጥሮ ቃላትን አሳብቆ፣

ድርድር የሌለው አገር ለመቀበል፣

‹አባይ› እወቅ አለኝ

እንቆቅልህ ሳይል፡፡

እሺ ግብፅን ውሰድ

ላንተም ይሻልሀል፣

ኢትዮጵያየንማ ራሱ ወስዷታል፡፡

# ገሀነብ

ከ'ሳት ሰባት እጥፍ

የሚያቃጥለው ፍም

ነበልባል ካለማ፣

እንኳን ቁር በረዶ

ውርጭ ቅዝቃዜ

የታለ ጨለማ?

# ፅናት

ሲወዘወዝ ሲናጥ በነበረው

ትዕግስት፣

የማዕበሉ ታጋይ ቅቤ ወጥቷል

አናት።።

(ምዕ የዛሬን አያድርግና)

# ጨቀየ

ድንጋይ ክበው ደራርበው

በላዩ ላይ ጭቃ መርገው

ከወራጁ ቦይ አውጥተው

በመሌ መርተው ወስደው

ሊያለሙ አትክልት ፍራፍሬ

ማሳ ገብተው በወሬ

እንደነዱት ተመርቶ

ቢከተልም ተጠማዞ

እርሱ ጥን'ሱን

የቀድሞውን ሀቅ አርግዞ

ወደ መሬት ሰርጎ ገብቶ

ደርቆ አናቱ ተለይቶ

ፍንጓል ከላይ እየታየ

ውስጡ በውሃ ጨቀየ።

# መከለያ

ከመንገዱ ዳር እርቃኗን
የመብራቱን ግንድ ታቅፋ፣
ልታጣፍጥ አዳሯን
የቆመበት ተቀላጥፋ፣
ብትመከር አሸንፋ፤
እምቢ ብላ ተመናቅራ፣
ሲፈስባት ያድራል ብርድ
ካስፋልት ዳር ተገትራ።።

ባይሆን ሱሱ ካሸነፋት

ያ ልማዷ ቅንዝሯ

ምናለ ብትሸፍነው

እንትኗ እንኳ እስከ እግሯ

ግዑዙ እንኳ ፌርማታዋ

የቸገረው መጠለያ

ፖሉ ለብሷል ማስታወቂያ

የ'ርቃን ገላው መከለያ።።

# የሆዳም ይትብሀል

ምግብ ላያሳጣን

ቃል ሲሰጥ ጌታችን፣

ተመልከቱ ከሚል

የሰማይ ወፎችን፣

ሀያ አራት ሰዓት

ምግብ ውስጥ ያለውን፣

እኛን ከወደደን

ነቀዝ ባደረገን።።

# ቃጠሎ

ስፖርት ባትሰራም

ባትችልም ቱኳንዶ

የቻይና ማርሻል አርት

ውሹና ጂት-ኩንዶ

ሰርከስና አክሮባት

ካራቴና ጁዶ

እጂ እግርህ ቢዝልም

ቢቆር ከበረዶ

ትምዘገዘጋለህ ትሆን እባብ ዘንዶ

እሳቱ ሲገርፍህ ወላፈን ከማዶ

ከሁለት ጭን መሀል

ጠባብ ሳር ቤት ነዶ።።

# ድሀ ተጋባኸ

ውስኪና ወይን ጠጂ ቡና ማኪያቶ

ብዙ የሚሻለኝ የሚጠጣ ሞልቶ

በየገባንበት ሻይ እየጠጣሁኝ

ኪስ እንዳላሳሳ ብየ ለሰጋሁኝ

ስሜን ቀሸሩና

ፊርሙዝ ብለው ጠሩኝ።።

# ንፅዕር

ብናስተውልማ ከራስ እስከ እግር

ባምሳለ እራሱ ፈጣሪ ሲፈጥር

ካፍንጫ ቀዳዳ ከጆሮ ጀምሮ

ዐይን፣ እጅ፣ እግር፡ ሁለት

አምስት አእምሮ

ሲያበጀን ፈጣሪ ሊያስተምር ብላቱ

አፍን አንድ አድርጓል

ከስነ-ፍጥረቱ።።

# ክቡር ዳኛ!

ቅዱሱን መፅሀፍ

ነክተው እንዲምሉ

ሶስቱንም ዋቢዎች

እርስዎ ያዛሉ

መጸሀፉ እንደሚል

እንደታማኝ ቃሉ

ሳያዩ ያመኑ

ብጹአን ከሆኑ

ሳያዩ መመስከር ምነው መኮነኑ?

## የቶፋ ሴራ

አባት ሲተርቱ

‹ባንዲት እልፍኝ› አሉ

ሁለት ጋኖችና

ብዙ ቶፎች ሳሉ…

ጋን መሆን ያማራት

አንዲት ቶፋ ቀብጣ

ዘዴ ስትዶልት

ከላይ ተቀምጣ

እሷን ጋን ለማድረግ

ሀሳብ አፈለቀች

ጋኖቹን አጋጭታ

ማሳበር አቀደች

ጋኖቹም ተጋጭተው

ከተሰባበሩ

ፍርክስካሽ ከሆኑ

ውሃ እማይቋጥሩ

ምንችት ትሆናለች

እውነትም ይሳካል

ጋኖቹ ሊጋጩ

እጂ ዘርግተዋል

በጃቸውም መዳፍ

ቁራጭ ጡት ይዘዋል።።

# ምሳሌ

ወፎች አባርሬ በጠጠር ባለቱ፣

ማማው ላይ እንዳለሁ

ተግ ሲል ጅረቱ፣

አንድ መስመር ሳነብ

መፃፉን ካናቱ፣

ለነገ እንዳናስብ ቃለ-መሰረቱ፣

የሰማይ ወፎችን

ይላል ተመልከቱ።።

አንቀጹን ጨርሽ

ቀና ስል በሀሴት፣

የምሳሌው ምስጢር

ገብቶኝ፣ ያነበብኩት፣

ማሽላየን አየሁ አዕዋፍ ወረውት።።

ከማማው ወርጀ

ወንጭፌን ቆርጬ

ጥየ ቆራርጬ፣

እርሻ ያፈራውን

ከወፎቹ ጋራ

ውልብኝን ለቅምጬ

ወፎቹ ሲነሱ ሲበሩ በተርታ
ያመቱን አዝመራ
ጭጭ አ'ርገው ባን'ዳፍታ
ጥማቴን ላረካ እኔም የለት ምሴን
ላሬን ብቻ እያሰብኩ
ባቋራጭ የነብሴን
ወደ ወንዝ ወረድኩ
ታቅፊ መጻ'ፌን።
ወንዙ ዳር አርፌ
አንቀጹን ስቀጥል
መፅሀፉ እንዲህ ይላል....
ጥረህ ግረህ ብላ
ከአሁን በኋላ!!

# ቅናት

ያርባ ቀን እድልህ
ላይጥልህ ወዴትም፣
አትልፋ አትድከም
ተኛ ላይብረሪም፣
ስማ!
ታውቃለህ አይደለም
ባልነግርህ ራስህን?
መሸምደድ ልሂቅነት አይደለም
አሰራው አንጎልህን!
ደሞ ምን ታውቃለህ?
ባዶ ነህ!

**ኤ፣ ቢ፣ ሲ፣ ዲ አይደለም**

**ጉብዝና መለኪያው**

**ከኛም ወዲያ ፉጨት**

**አፍን ማጣመም ነው!**

*(ያላስኮረጅን ቀን ከፈተናው በኋላ*

*የሚጠብቀን ውርጂብኝ)*

# እሽጌ መሸታ¡

ማታ
በጨረፍታ
ውልብታ
ምልከታ

ታይታ
ተጎንጭታ

እምቢልታ
ሲመታ
እሩምታ
ሁካታ
እስክስታ

ጠጥታ
ጠጥታ
ጠጥታ

ተላፍታ
አላፍታ

አውጥታ
ተወጥታ
ወስልታ
ለአፍታ
ተሳስታ
አምሽታ
መጥታ

ለአንድምታ
ፈርታ
ተኝታ
ቆይታ

ተጎትጉታ
ነቅታ
በርጋታ
ተነስታ

ተጀክታ
ቱታ

ከታታ
መኝታ
ተጋጭታ
በቴስታ

አንርታ
አንርታ

ህቅታ
ህቅታ

ሻታ
ሻታ
ሻታ

እጭ... እቱ
እህቱ!!

# ተመን

ባለወጀድን ጨለማ፣

ባለተቅሊጥን ማማ፣

ባለድጎማን ሻማ፣

ብለህ ሰውን መሰየምህ፣

አንተ ድጎማ ስላማረህ፣

ከሆነ፡

ማማ ላይ የወጣ ሻማ፣

ቀን ሳይበራ በጨለማ፣

ባለወጀድን አባሮ ባለድጎማን፣

አያዛልቅምና ያለተቅሊጡ ተመን፣

ባይጠቅም'ንኳ አይጎዳም
የምመክርህ፣
ጆሮ ስጠኝ ወገኔ
ሻማነት ይቅርብህ፣
በርተህ በ'ርተህ ትቀልጣለህ፣
ስጋህ አልቆ አ'ሮ አንጀትህ፣
ስትጋደም ውኃ ሁነህ፤
ብርሀንህን ስታጣት፣
ባለወጀድ ይወስዳታል
ተቅሊጥህን ሊደጉማት፣
ካንተ 'ርቃ ድጎማዋ
ስትሆን ሻማ፣
ተቅሊጥህም በተራዋ
ትቀልጣለች በጨለማ።።

# ማዶና ማዶ ነን

ተወልደን ስናድግ አብረን ቦርቀናል
ካፋፍ በታች ወርደን ብዙ አሳልፈናል
ካሸዋው ተራግጠን በውሃ ተራጭተናል
አድገንም ዋኝተናል አብረን አስግረናል፤
ግና...
ወንዝ አብረን ብንውልም እንለያያለን
ወደ ማደሪያችን ሲመሽ እንባጃለን፤
ከቦታው ባንኖር ሀገር ብንለቅም
አይሻርም ውሉ እስከምታልፍ ዓለም
የኛም **ተመን** ያንተ: ያንተም የኛ አይደለም
ማዶና ማዶ ነው አደናግሮ አያውቅም::

## እንዳያስቸግረኝ¡

ትምህርት ቤት ስቀር፣
ቀጠሮ ላከብር፣
እጅግ አሳሳቢ ወሳኝ ጉዳይ ኑሮኝ፣
ስልክ ስጠባበቅ እስኪደወልልኝ፣
ሰዓታት ተሻግረው
ስድስት ሰዓት ሆነ፣
ተማሪውም ወጥቶ እየተበተነ፤
ስልኩ ተደወለ በቀጣሪው ቁጥር፣
መገናኛ ቦታ በደረጃ ዝርዝር፣
ባ'ማራጭ ካፊዎች ሆቴል ስደረድር፣
እንዳያስቸግረኝ የተጨናነቀው፣
ትምህርት ቤት ነበር
ሊያገኘኝ ያሰበው።።

(የዘመናችን ሴማሪዎች)

## ገድሚ

መርጠሽ እንዳላጣሽ ባይንሽ የሚሞላ፣
ምራጭም ቸገረሽ ለስሜት ለገላ፣
ሀብታም አገባለሁ በሚባል ይትብሀል፣
አርባ ሻማ አበራሽ በትዳር እደር ዋል።።
ሰውየውም ቢሆን ተስፋ እምታደርጊው፣
ልጃገረድ እንጂ እምታስደስተው፣
እነ አንቺን አይደለም ሲያድን
የሚውለው።።
በኋላሽ ተወልደው
ወልደው አሳድገው
ስታይ ከምትደሚ፣
እድሜሽ ይመጥናል
እኔ ልወቅልሽ
ዝም ብለሽ ገድሚ።።

(ገድሚ፦ ገዳም ግቢ ማለት ነው)

# ቆጨሽ እንዴ

ከቅንድብሽ በታች

ያከተው ደመና፣

ባፍንጮ ተራራ ጉሙን አጎመና፣

ዝናቡን ለቀቀው

ዐይንሽ መብረቅ ጥሎ፣

የሰበርሽው ልቤን አላየኝም ብሎ።።

... ገብቶኛል!

# አንሽና ተነሺ!

ስትቀመጪ ስትተኚ
ተዛመሽ ስትቆሚ
ከልብሽ ላትስቂ ስትሸኮረመሚ
የሌለሽን ውበት
ካሜራው ላይሰጥሺ
ጊዜና ገንዘብሽን
በከንቱ ስትጨርሺ
እድሜሽ እስኪሸብት
ግራ እንደተጋባሺ፣
በዝምታ ከማልፍ
እቅጩን ልንገርሺ፣
ከልብሽ ሳትስቂ
ሳይገለጥ ውስጥሺ፣
ሙሉ ፎቶና ባል
መቼም አይወጣልሺ።።

# እሳቸው

ጫማቸውን ሊጠርግ
መቀመጫ ለቆ
ያስቀመጣቸው ሰው፣
እያለ ሊስትሮው
ፈትቶ የሚጠርገው
ወልውሎ የሚያስረው፣
አፍንጫ እሚያስቆርጥ
ጫማቸው ሳያንሰው፣
ቦርጫቸውን ዘለው
ጫማ አስራለሁ ብለው፣
ሲያስነጥሱት ዋሉ
ምስኪኑን ሊስትሮ
ፈሳቸውን ለቀው።።

# ራስ

ወላጅ ወንድም እህት
መስታዎት ነበሩ፣
ኮሌታ ፊት ጠጉር
አይተው ሲያሳምሩ፣
ይመስል የነበር አባቱን በመልኩ፣
በባህርይ በ'ምነት በር'ዮት ሲለኩ፣
ተመንደግ ያሉት ልጅ
እራሱን አስቻለ፣
ክብ መስታዎትም ከበሩ ሰቀለ፣
ከመስታዎቱም ጋር
ጠጉሩን ሙጥኝ አለ፣

ከመስታውቱም ውስጥ

ይህን አስተዋለ፣

ሲያልም እያደረ ሲያስብ እየዋለ፣

ጠቆረ ከሰለ፣

በራሱ አደረ ዳበረ በሰለ፣

ፊት እምነት ባህሪው

ᵎራሱን መሰለ።።

# ዝም በል!

እንኳን ከስብሰባ
ወጥቸ ከመድረክ፣
ለቆኝ መንቀጥቀጤ
የእጂ እግሬ መብረክረክ፣
ልናገር ሀሳቤን ስሜቱን ከውስጤ
ለቡድን ስራ እንኳ አጥቻለሁ ቢጤ
መግባባት መናገር
ሳይኖረኝ የቤት ልምድ
እንዴት እሰራለሁ
ከሰው ጋር በገሀድ?
የክፍለ ዘመናት

ያ'ባቶች ታሪክ ጀብድ

ሲወሳ ሲወራ በዘልማድ ዘመድ

ከንፈራን ሳላቅቅ ገና ልናገር ቃል

ዝም በል! ዝም በል!

ዝምምም... በል!!

እያሉኝ አድጌ ሰው ባፍር ብፈራ

ምኑ ነው እሚገርም ዛሬ ባላወራ?

ጠረጴዛ ወንበር

ባይኖር መፃፍ ማንበብ፣

ቤተመፃ'ፍት ነው የገጠር ቤተሰብ።

ኧረ ባክህ ዝም በል!

## የምርጫ ሰሞን ክስተቶች

ከተራራው ማዶ
ዋይታ ጩኸት ሰምቶ፣
ሳጂን አለቃቸው
ከፊት ከፊት መርቶ፤
በተ'ስኪያኑን አልፈው
እንዲቆሙ አድርጎ፣
ታጣፊ ክላሹን ጥይቱን ደግድጎ፤
ከእሪታው መሀል ገብቶ ሊያረጋጋ፣
ሲያየው ተሰልፎ ህዝብ እየተላጋ፣
ሀሎ! ሀሎ! ሀሎ! ይሰማል ይሰማል?
ባስቸኳይ ባስቸኳይ
ይምጣልን ሌላ ኃይል!

መቶ አለቃው ፈጥኖ አዲሱ ተሿሚ፣
ኃይሉን አሰልፎ ስልጣኑን ጠቋሚ፣
የዋሻውን ጨኽት እሪታውን ቀርቦ፣
ሲያያቸው መምሬን ኮተቱን አንግቦ፣

አንዲቱ ጠብታ ግንባሩ ላይ አርፋ፣
እሪታ ጀመረ ሳይጠብቅ ወረፋ፣
የሪታው አንድምታ
የቦታው ምስጢሩ፣
እንኳን በጅልግ ክላሽ
ቢያዝ ዲሞፍተሩ፣
እሪ ነው የሚሉ፣
ያ ያላቸው ሁሉ፣
ታምር ነው ፀበሉ።።

(ፖሊሶች ለጥቂት ዓመታት እንደዛ ነበሩ)

## ክንድ ርቀት የለም!

አላማጣ ሁኖ ይታያል ሁመራ
በመካከል ያለው ሽንተረር ተራራ
ከልሎት አያውቅም
ክንድ ርቀት የለም
ታዲያ ምን ያደርጋል የቆጡንስ ማለም
መስፈሩን ብቻ እንጂ ልክ አዋቂ የለም
እንኳንስ ጠገዴ ኮረም ተሳደበ
በቀን ተራራ ላይ ዘልቆ ለታዘበ፡፡

## የዘንድሮ ሌባ

የድሮማ ሌባ ፍንጁን ከተያዘ
በጥፊ ሲመታ እየደነዘዘ፤
ይቀጣል፡ ይማራል[1] ይቅር በሉኝ ብሎ
ድጋሜ ላይገኝ በዚህ ስራ ምሎ…
ባማን ይለቀቃል ተመክሮ ተንቆ
እንኳን የኪስ ገንዘብ ወይፈን በሬ
ሰርቆ።

የዛሬማ ሌባ … ፍንጁን ከተያዘ
እንኳን ሊደነዝዝ እንኳንስ ሊመታ
እምቧ ዘራፍ! ይላል በአረር እሩምታ
….
ጥፋት ማመንና ማሩኝን መች አውቆ
እንኳን ወይፈን በሬ ተራራን ደብቆ፣
ግማሽ ሀገር ሰርቆ።

[1] ምህረት ይደረግለታል፤

# የወል ሚስት

**ፍጥረተ - አዳምን**

**ካስተዋወቀችህ**

**ወንድሜ ነው ብላ፣**

**ባልነትክን እርሳው**

**አንተም ወንድሟ ነህ**

**ተዋወቅ ከሌላ።።**

# ኢትዮጵያ

እስላሎ ጎንደር መገን ሊማሊሞ

አናቱ ላይ ቁስ ነው ወገቡን አጣሞ

እስላሎ ራያ የኮረም ጎዳና

እንኳን ፈረስ በቅሎ አይወጣው
መኪና

እስላሎ ወሎ ድልብና ደገራ

መንገድ እንደ ገመድ እጅ እንደ
ባንዲራ

እስላሎ ሸዋ ዚግዛጉ ከሚሴ

ከኮምቦልቻም በላይ እስኪደርሱ ደሴ

እስላሎ ሐረር የድሬው ደንገጎ

መኪናን በዜሮ አውታንቲን በኮንጎ

ጠመዝማዛው ጀምጀም ሜዳም
ወጀምጃማ

አይንን በጉም ጋርዶ ዳመናው
ጨለማ

እስላሎ ደቡብ ሲዳፉ በቦኻቦቡር

ቡታጂራ ድረስ ሲወረድ በቀመር

ማየት ማመን ሊሆን ተሰርቶ ዘቢደር

ኧረ ብቻ ስንቱን ጥምዝምዝ

መንገዱን

ተሟዙረው አይተው ባራቱም ማዕዘን

ሲያዩሽ ወደኋላ ሊቃኙ ትዝታን

ሾፌሩ አባትሽ ኢትዮጵያ አሉሽ

አንችን።።

(ለጠማሚት!)

# የስራሺን ይስጥሽ

ስምሽን ከጨረቃ ውበትሽን ከጮራ

አስበልጠው ሲያወድሱሺ ሲወራ

መቀመጫ ዙሪያ መርገጫሽ በሙሉ

እንደው ሁለመናሽ ኤዶም ገነት ሲሉ

የሳሉልኝ አንቺሺ በእንቁ አሸብርቆ

ስጣደፍ ስቻኮል አይሽ ቀኔ ርቆ

ሱባኤ ጀመርኩኝ ጾምም ያለልምዴ

በምግብም ፋንታ ተሞልተሽ በሆዴ

አንቺን ስል ከርሜ ስሆን የምንግዴ

ቢወራም እንከንሽ ህፀፅሽ አንዳንዱ

ጆሮ አልሰጥም ብዬ ሰውማ ልማዱ

ማንም አያገባው ያንች ልሁን ብቻ

ይውገሩኝ ይስቀሉኝ ልሁን መዛበቻ

ብዬ እንዳልፀለይኩኝ
እንዳልተማፀንኩኝ

አየሁሽ አየሽኝ

ታዘብኩሽ ታዘብሽኝ

አሸሺኝ እንደ ገብስ ወቀጥሽኝ እንደ አጃ

ኤዶም ገነት ያልኩሽ ሲኦል ሁነሽ
ፍርጃ

አንቺን ስራ አድርጌ ሁሉን ነገር
ትቼ

መንቀሳቀስ ዙረት ከተማ

ረስቼ

ፀባየኛ ልጅ ነው ጎበዝ ነው
ትምህርቱ

ተብሎ እንዳልተወራ ብርታቱ
ውጤቱ

አንቺ ተረት አርገሽ ሳይነጋ ምሽቱ

የሆንኩትን እኔን አ'ርገሺኝ የጥንቱ

ልኖር አስገደድሺኝ አንገቴን ደፍቼ

ዝናዬን ውጤቴን ጓደኛም አጥቼ

ለዲግሪ መጥቸ በህንድ አሰዳቢ

የ'ጂሺን አይንሳሺ 6 ኪሎ ግቢ።።

(አአዩ 2001 ዓ.ም.)

# ሰገጤ

የትምርቱ አውራህ በጋው እንዳለቀ

የሺርሺሩ ቀን እንደተጠበቀ

ከች! አለ ዕለቱ እንደተናፈቀ

ላንጋኖም ልንሄድ ጉዞው ተረቀቀ

አስፈላጊው ነገር ሁሉም ተሰነቀ

የጉዟችን ቀንም ደስታን ፈነጠቀ

ባህሩ ይመቻል ሁሌም ባልደረቀ

እያልን ልንዋኝ ልብስም ተወለቀ

አንደኛው ጓደኛ ሀሳብ አፈለቀ

‹‹አንዋኝም!›› አለ በማየት አለቀ

ሁላችን ስንስቅ ስሜቱን ደበቀ

እንደገባው ሁኖም በኛ ተሳለቀ

የእፍረት ወኔውን እየተናነቀ

ሱፍ እንደለበሰ ዘሎ ተ ዘ ፈ ቀ !

# አሳድጎ ለሰው

በእቅፉ አምጥቶ

ተክሎ አሳድጎ ኮትኩቶ

አለምልሞ ውሀ አጠጥቶ

ሳይጠግባት

ያሳደጋት

ቀለም መዓዛዋን

ጽጌረዳዋን

ገና እንቡጥ አበባዋን

አስቀመጧት ቀጥፈው

በብርጭቆ በሚያደርቀው

አለያዩዋት ካሳደጋት

ውሃ ፈውሷን ካጠጣት

ለፍቶባቸው ደክሞባቸው

ሲያይ ተጥለው

እንቡጥ አበቦች ደርቀው ወድቀው

ከልብ ነው እሚያስከፋው

አሳድጎ መስጠት ለሰው፡

እስከዛሬ ያላወቀው ፍጹም ግራ የገባው

ከመኮትኮት ባሻገር ማቀብ ብቻ ነበር ስራው

ተገልጦለት የአበቦች እንቡጥ ህይወት

ምስጢሩ ቢዘገይም በሰው ህይወት ተምሳሌት

ካሳዳጊ'ጂ ከወጡ ልጆቻችን ተማሮቹ

ባድራሻችን ይመጣሉ

በሱስ ደርቀው እንቡጦቹ።።

# አማላይ

ድምጽሽ እንደሚያንበረክክ

ቁመትሽ እንደሚማርክ

ፍቅርሽ እንደሚናደፍ

ዓይንሽ እንደሚጋረፍ

እያወቅሁ የቀረብኩሽ

ዓይን ገርፎኝ

ድምጽ አንበርኮኝ

ፍቅር ነድፎኝ

ስለማያውቅ ልፈትንሽ

‹አፈቀርኩሽ› ብዬ ጠየቅሁሽ

ከልቤም ቦታ እንዳለሽ ነገርኩሽ

ልብሺን ልማርክሺ

አንቺ ግን እንዴት አወቅሽ?

መግቢያ መውጫው ሳይጠፋሺ

አዳምጠሺ ታዝበሺ አስተውለሺ

ጨንራ ጉበት ሳንባ... ዋቢዎቹ

እንዳይለዩሺ

ብርሀን በሌለበት ምሽት መጥተሽ

እኔን ባዚም አታለሽ

ልቤን አውጥተሽ ወሰድሽ

ሳትነድፊ ሳትገርፊ ዘረፍሽኝ

እኔ ያንችን አልፈልግም

የራሴን ልብ መልሺልኝ፡፡

# ደባል

ድመትና ዶሮ ቤት ተከራዩና

ብዙ ዘመን ኖሩ በሁለት ቀጠና

ኑሮው ተወደደ ብለው ዳለቡና

መተማመን ሳይኖር ሳይጠና ጉተና

ጎጆ መሰረቱ ሊኖሩ ቀበና።

ሁልጊዜ አያ ድመት ሲሄዱ ገበያ

የሚገዙት ዕቃ የድር መወያያ

ዋጋው እሚለየው በሰላሳ ሀያ!

ከለታት አንድ ቀን ዶሮ ተቆጥታ

ገበያ ልትሄድ ቅቤ ተቀብታ

በር ላይ አገኛት ደሜ አያ ብላታ¡

‹‹እህል ቤት ልጠይቅ›› አለችና ዶሮ

ክንፏን አረጋግፋ መንጠቅ በስተጓሮ

አህል ቤት ስትደርስ ሁሉ ነገር ንሮ!

እንኳን ነጭ ስንዴ ዘንጋዳም ጨምሮ

ደንገጥ አለችና ብላ ‹‹ወይ ዘንድሮ!››

ቀድማ እንደማታውቅ

እንዳልሰማ ጆሮ

ሁለት ስንዴ አንስታ

ላክ ወደ ጉሮሮ

ሻጭ ምጥምጥ አጂሬ

ፈልጎ አምባጓሮ

‹‹መቶ ብር ክፈይ!›› ፊቱን አኮሳትሮ

በ‹‹አልከፍልም… ክፈይ!››

ትንሽ ተከራክሮ

ምጥምጥ እያዛጋ ተጠጋት አንጋሮ

ካክ! ብላ ስትዘል በክንፏ ጠፍሮ

ኮልኮል አረገና ብብቷን በክሮ

አቀለጣጠፋት በግድግዳው ዙሮ

አዲያ ቅሬ ጠሪው

ጎልማሳ አይጥ ነበር

የ'ህል ቤት ዘበኛው ድሮ ሳይባረር

ጡሩንባውን ይዞ አይጥ ቅሬ ሲለፍ

ድመቱ ሰማና የንግስቱን ማለፍ

ምን እንዳጋጠማት አጥብቆ ጠየቀ

አይጥም በፍራቻ እየተሳቀቀ

ምጥምጥ ያረገውን

ለድመት ሲያረዳው

ቅሬ ለፋፊውን ሲጥ አድርጎ በላው

በደም ፍላት ስካር ረሀብ ተጨምሮ

ድመት ስላቃተው

ከአላዥር አምባጓሮ፡፡

እንግዲህ እንዲህ ነው ችግሩ በከፊል

ከማይመስሉህ ጋራ ለመኖር

መዳበል፡፡

(አላዥር፡ ምጥምጥ ማለት ነው)

# የኔ ምቹ

እግሬ እስኪነቃ ብዞር በዚች ዓለም

እንዳንቺ አይነት ‹ምቹ› የትም

አላገኝም።

ወጥቸ ስጠፋ ከባዶ ቤት ትቸሽ

እኔ አገር ሳደርስ

አንቺ ካልጋ ‘የዋልሽ

ያሻኝን ብሰራ ምንም ሳይሰማሽ

… በደከመኝ ጊዜ ትደግፊኛለሽ

በታመምኩም ጊዜ ታስታምሚኛለሽ

ሳነሳ ስጥልሽ ደስም ሲለኝ ሳቅፍሽ

የልቤ ትርታ አዳማጭ አንቺ ነሽ፡፡

ከልቤ ‘ምወድሽ እስኪወጣ ነፍሴ

የምቾቱ ዋልታ አንቺ ነሽ ትራሴ፡፡

## እግረ - ተከሉ እረኛ

ገና ጡቱን ሳይጥል

ቁሞ መሄድ ሳይችል

በረሀብ በ'ርዛት ኑሮን ይጋፈጣል

የቤቱን አቅጣጫ

መንገድ እንኳን ሳያውቅ

አጭር ልምብጭ ይዞ

ይወጣል ሊጠብቅ

ገና ... እግረ ተከሉ

መሮጥ የ'ማይችለው

ፍየል ይጠብቃል

እንዴት ሊመልስ ነው?

ዝናብና ውርጩን ፀሀይ ወበቅ ችሎ

ከብት ይዞ ይመጣል በዋለበት ውሎ

ድክምክም ... ብሎት ተርቦ ተጠምቶ

ሲገባ ወደ ቤት ለመመገብ ጓጉቶ

እራት ይጠብቃል ገና ቡን ተፈልቶ

እራቱንም ሳይቀምስ

እንቅልፍ አሸንፎት

ከወለሉ ያድራል

ካልተነጠፈበት።።

# ባገሩ መቀበር

ምን አይነት ዜማ ነው
ይሄ ውብ ሀገሬ
ኑረን ባናየውም ደርሶናል በወሬ፣
እናት አባት ቢሞት ባገር ማልቀስ
ቀርቷል
መከበርም የለም አንገት መድፋት
ነግሷል
ኗሪው ተፈናቅሎ ወራሪው
ደርጂቷል
ግራ የተጋባው ወጣት ይሰደዳል
በየደረሰበት እንደሳር ይረግፋል
ሀገር ስለሞተች ወዴት ይደረሳል?
ባገር መቀበርም ለካ ይናፍቃል!

ከዚያም መጣሁ ልሰራ

ምንም ነገር ሳላጣራ

ይኖር ዓይኖር ስለ ስራ

ማን ነግሮኝ ምን ሰምቸ?
በደፈናው መጥቸ

እንዴያው እንዳመጣጤማ

ሰው ባይኖረኝ ተቀባይ ከከተማ

ምን ይበቃኝ ነበር? ልጉላላ?

ወቸ ጉ...ድ! አሉ አባ መላ

መጥቸም ሰው ማስቸገር

ለ'ኔ አስቤዛ ወጭ መጨመር

እኔ አሳቤ ሌላ ነበር፡-

እየተዝናናሁ ልሰራ
ትርፍም ገንዘብ ላፈራ
ቤተሰብም ልመራ

ብዙ ገንዘብ አካብቸ፣

መላ ወጨን ረስቸ

ልኖር ነበር በድሎት
ሆነና ... ምን ይደረግ የቆጥ ምኞት

ሌላ'ያምጣ ፈጣሪ

ገንዘብማ በዋል ቀሪ

ዋናው ለሰው

ጤና ነው

እልና ብዙ አስቤ

በሀተታው ተሳስቤ

ድንጋጌው መቀመጥ

ያ' ሁሉ ቀርቶ መሯሯጥ

ያውም ደግሞ ትልቅ ፍራት

ገብ ብሉ በየዕለት

ወጥቶ መግባት 'ማይዘነበት

ጥርጊያው ሁሉ የቁማር ቤት

እኔም ሰለቸሁ ዛሬስ

የሚበላንም ጉርስ

የሚዘገንንም እፍስ

ምግብ አልመርጥ እንደፈረስ

እርጥብ ደረቅ ሳግበሰብስ

በደቂቃም ሆድ መዳበስ

ወይ ፈተና! መች ያልቅና

ይቀጥላል ሁሉም ገና፡-

ሳልችል ስራ ገባሁና

አዛኝ መጣ ችግር ጠና

እዛ ሂደህ ወደዚህ ና!

ሁሉም ትዕዛዝ በአፈ-ነጩ ጠላሁና

ከጧት - ማታ ደፋ ቀና

ብሎ መስራት ይላልና

ከየት ይምጣ እንደገና

ያልለመድኩት ጥንክርና

ባልተማርኩት እንግልጥርና!

(እንግልጣር-እንግሊዝ፣ እንግልጥርና-እንግሊዝኛ)

**አ ለ ቀ ች !!!**